# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity



efdpu@aol.com www. Finote.org



**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

*መጋቢት 10 ቀን 2003 ዓ.ም.*

**የወያኔ ፖሊት ቢሮ አባሉ በመለስ ትዕዛዝ ተነሳ፤**

**በመከላከያና በፌዴራል ፖሊስ ውስጥ በምስጢር የአንድ ወገን ሰዎች ቁልፍ ቦታ እንዲይዙ ተደረገ፤**

**ባድመ ላይ መስዋዕት የከፈሉት ዜጎች ከንቱ ሆነ፤**

**ወያኔ አሁንም ታሪክ እየደለዘና ጨርሶ እያጠፋ መሆኑ ታወቀ፤**

የወያኔ ቡድን በአንድ ወገን ላይ ብቻ በጀመረው ምንጠራ የኦህዴድ ካድሬዎች እየታመሱ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ።

ለዓለም መንግስታት እና ለህዝቡ ለማስመሰል ሲል በአንድ ወገን ላይ ብቻ የምንጠራ ዘመቻ የጀመረው የወያኔ ቡድን አዳዲስ እና ከተማ አመጣሽ የሆኑ የኦህዴድ ካድሬዎች ላይ ብቻ አዲስ ዘመቻ መጀመሩ እያነጋገረ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

ከተራ ንግድ ስራ እስከ ኩባንያ ባለቤት ለመሆን የበቃችው የመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን እና የወያኔው መሪ መለስ ሎሌ የሆኑት የጦር ጄኔራሎች በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ከሀገሪቱ ህዝብ ላይ ዘርፈው እያከማቹ ከመሆኑም በላይ በቦሌና በተለያዩ ቦታዎች ቪላ ቤት እና ህንፃዎች አሰርተው እያከራዩ ባለበት በዚህ ወቅት ጥቂት የወረዳ እና የቀበሌ ሹማምንቶች ያውም በአንድ ተለጣፊ ፓርቲ ካድሬዎች ላይ ብቻ የምንጠራ ዘመቻ በማድረግ ወያኔ እራሴን እያፀዳሁ ነው እያለ መገኘቱ ለማስመሰል እያደረገው መሆኑን የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አጋልጦዋል።

የህዝብን ገንዘብ እና የሀገርን ሀብት ቀን በግላጭ ለሌት በድብቅ ሲዘርፉ የኖሩት የወያኔ የጦር ጄኔራሎች ዛሬ በሀገር ውስጥ አንቱ የተባለ ቱባ ባለ ባለሀብት ለመሆን የበቁ ሲሆን አዜብ መስፍን

በበኩልዋ ከተራ ንግድ ጀምሮ እስከ ኩባንያ ባለቤት..... ከመንገድ ስራ ተቋዋራጭ ባለቤትነት እስከ መኪና አስመጪነት .......ከቡና ንግድ እስከ ህንፃ አከራይነት ወጥራ እየሰራች በህዝብ ገንዘብ እስከ አንገትዋ ድረስ ተዘፍቃ ያለች መሆኑ ቢታወቅም በኦህዴድ ካድሬዎች ላይ ብቻ ምንጠራው ማነጣጠሩ ከፖለቲካ ጋር የተገናኘ ሳይሆን እንዳልቀረ የሚያመለክት ነው ሲሉ ምንጮቹ ገልፀዋል::

ከቅርብ ቀናት ወዲህ በአዲስ መልክ ዘመቻ የተጀመረባቸው የኦህዴድ የወረዳና የዞን አመራሮች ከ120 በላይ የሚሆኑት ተይዘው አስኮ አቅራቢያ በሚገኘው ሳንሱሲ ተብሎ በሚጠራው እስር ቤት ታጉረው የሚገኙ ሲሆን በቅርቡም እነ አባዱላና ሌሎች ተመሳሳይ የኦህዴድ ባለስልጣናት ከዚሁ ጋር በተያያዘ ወደ ዘብጥያ ሊወርዱ እንደሚችሉ ምንጮቹ ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል::

ከመሬት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ተብሎ ከአዲስ አበባ ዙሪያ ጀምሮ እስከ ናዝሬት..... ከዝዋይ ጀምሮ እስከ ሻሸመኔ..... አልፎ ተርፎ ሆለታና ሰንዳፋ የነበሩት የወረዳ ባለስልጣናት ከያሉበት ጆሮዋቸውን እየተያዙ በሳነሱሲ እስር ቤት ከመታጎራቸውም በላይ ማታ ማታ ከፌዴራል ፖሊስ በተላኩ መርማሪዎች በኤሌክትሪክ መመርመሪያ ማሽን እያሰቃዩዋቸው ያላደረጉትን አደረግን እያሉ ሲለፈልፉ እንደሚያድሩም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

ከመሬት ዘረፋ ጋር ነው ተብሎ እስር ቤት ገብተው እየተሰቃዩ የሚገኙት የወያኔ ቡድን አጫፋሪ እና አጨብጫቢ የነበሩት የኦህዴድ ካድሬዎች በምርመራ ወቅት ከማን ከማን ጋር ሰርተሀል? ለማንስ ሰጥተሀል ተብለው ሲጠየቁ አብዛኞቹ ለጄኔራል ሳሞራ የኑስና ለዘመዶቹ .....ለሌ/ጄ/ል ታደሰ ወረደና ዘመዶቹ..... ለ/ሌ/ጄ/ ባጫ ደበሌና ጉዋደኞቹ....... ለ/ሌ/ጄ/ ሳዓረ መኮንን እና የቅርብ ሰዎቹ.....በማለት የነበራቸውን ቅርበት ቢዘረዝሩም መርማሪዎቹ ግን እነሱማ አጥንታቸውን ከስክሰው የሀገር ዳር ድንበር እያስከበሩ ነው ስማቸውን አታንሱ እየተባለ እንደ አህያ እየተረገጡ መሆኑንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በተለይ የሰበታ ከተማ ከንቲባ የሆነው ሽመልስ የተባለው ግለሰብ በምርመራ ወቅት እንደተናገረው ከሆነ ከመለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ጋር ቅርበት እንዳለውና ለአበባ እርሻ የሚሆን እጅግ ሰፊ መሬት ያለ አንዳች ክፍያ በነፃ እንደሰጣት ገልፆ ከአባዱላ ገመዳም ጋር በምስጢር ሲሰራ እንደነበር በመናገሩ ለብቻው ተነጥሎ እንዲቀመጥና ዳግመኛ ይሄንን መስጢር እንዳያወጣ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጠው የጠቆመት ምንጮቹ ቤተሰቦቻቸው እየሄዱ እንዳይጠይቁዋቸውም ሆነ ምግብ እንዳያስገቡላቸው መከልከላቸውን ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በቅርቡ በኦህዴድ የማዕከላዊ ኮሚቴና ከፍተኛ ባለስልጣናት መሀከል በተደረገ ግምገማ ላይ ከ9 በላይ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከኃላፊነታቸው የተነሱ ሲሆን ገሚሶቹ ክስ ተመስርቶባቸው ወደ ዘብጥያ ሊወርዱ በተዘጋጁበት በአሁኑ ሰዓት ዘላለም ጀማነህ የተባለው የወያኔ የፖሊት ቢሮ አባል በሙስና ይሁን በፖለቲካ አቋዋሙ ባልታወቀ ሁኔታ ከስራ አስፈጻሚነቱ እንዲነሳ መደረጉ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በመስከረም ወር መጀመሪያ አዳማ ናዝሬት ላይ በተደረገው የወያኔ ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ነባሩን አንስቶ በአዲስ መተካት በሚል ተተኪ ናቸው ተብሎ ሲወደሱ ከነበሩት እና በመለስ

ሲሞካሽ የነበረው ዘላለም ጀማነህ ድንገት ሳይታሰብ ከፖሊት ቢሮ አባልነቱ በምስጢር እንዲነሳ ከመደረጉም በላይ ከነበረበት ቦታ ተነስቶ የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ እንዲሆን መወሰኑን ምንጮቹ አስረድተዋል።

ከወረዳና ከዞን አመራር የኦህዴድ ካድሬዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት የነበረው ይሄው ዘላለም የተባለው የወያኔ ተለጣፊ ግለሰብ ባለፈው ሳምንት ናዝሬት ላይ በተደረገው ግምገማ ስሙ ሳይነሳና ሳይተች ያለፈ ቢሆንም በምስጢር መለስ ዜናዊ ቢሮ ተጠርቶ በተሰጠው ማስፈራሪያና የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ ከፖሊት ቢሮ አባልነቱ እንደተነሳ ምንጮቹ አጋልጠዋል።

የኦህዴድ ካድሬዎችን መታሰር ተከትሎ መለስ ዜናዊ የኦህዴድ የፖሊት ቢሮ አባሎችን ብቻ በቢሮው ጠርቶ በራሳችሁ አትተማመኑም...... የተሰጣችሁን ኃላፊነት በአግባቡ አትወጡም...... ዘረኝነት ያጠቃችሁዋል ......ቆሻሻ ላይ አርፎ እንደመጣ ዝንብ ሳትመርጡ አሰስ ገሰሱን ታግበሰብሳላችሁ.....የፖለቲካ አቋዋማችሁ የጠራ አይደለም ......የማስፈፀም አቅማችሁ ደካማ ነው .... እያለ ከፍ ዝቅ አድርጎ የሰደባቸው መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በተለይ ዘላለም ጀማነህ የተባለውን የፖሊት ቢሮ አባል ከሌሎቹ በተለየ መልኩ የስድብ ናዳ ሲያወርድበት እንደነበርና በመጨረሻም ብዙ ስንጠብቅህ በአጭሩ ታጥፈህ አገኘንህ ለዚህ ደግሞ አስፈላጊው ቅጣት ይሰጥሀል በማለት ሲያስፈራራው እንደነበር የጠቆሙት ምንጮቹ በመለስ ስድብ የተደናገጡት እነ ሽፈራው ጃርሶ ያልተጠየቁትን ሲዘላብዱ እንደነበርም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በሀገሪቱ ከፍተኛ የመወሰን ስልጣን አላቸው ከተባሉት 36 ሰዎች መሀከል አንዱ የነበረው የኦህዴዱ ዘላለም ጀማነህ ከወያኔ ፖሊት ቢሮ አባልነት እንዲነሳ መለስ ዜናዊ ብቻውን ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን ለግዜው የክስ ፋይሉ እስኪዘጋጅ ድረስ በክልሉ ግብርና ቢሮ ተመድቦ እንዲቀመጥ መደረጉንም ምንጮቹ አብራርተዋል።

የወያኔ ተለጣፊ ኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት እና ከተማ አመጣሽ ካድሬዎች ላይ ፊቱን ያዞረባቸው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጥብቅ ግምገማ እንዲደረግ በማዘዝ ብዙዎቹ እንዲባረሩ የተደረገ ሲሆን በቅርቡም በእነ አባዱላ ላይ ሰፊ የማጥቃት ዘመቻ እንደሚጀመር ምንጮቹ ጠቁመዋል።

አባዱላ ከዚህ ቀደም በቦሌ አቅራቢያ የሚገኘውንና ከህዝብ ላይ ዘርፎ የሰራውን ቪላ ቤት ለድርጅቱ ሰጥቻለሁ ብሎ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ይህም በግምገማው ላይ እንደሚነሳና ከሌሎች ችግሮቹ ጋር ተደማምረው ወደ አዘቅት ውስጥ ሊከቱት እንደሚችሉ የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አለማየሁ አቶምሳ....የአዲስ አበባ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳና የመለስ አማካሪ ሙክታር ከድር በተሰኙት ጋላቢ ፈረሶቹ አማካኝነት ኦህዴድን እያመሱት መሆኑን አክለው ገልፀዋል።

በአሁኑ ሰዓት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በወረዳና ቀበሌ ጭምር ምንጠራ እየተደረገ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ስራ ሙሉ ለሙሉ የቆመ ሲሆን አንዳንዶቹ ካድሬዎች ባገኙት አጋጣሚ ወደ ውጭ ሀገር እየጠፉ እንደሚገኙም መንጮቹ አብራርተዋል።

በናዝሬት በተደረገው ግምገማ ላይ አንዳንድ ካድሬዎች ከእኛ በላይ የሀገሪቱን ሀብት ግጠው ቱጃር የሆኑት የህወሀት ሰዎች እያሉ እነሱ ምንም ሳይባሉ በእኛ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ዘመቻ መከፈቱ ከጀርባው ያዘለው ትልቅ መልዕክት አለ በማለት ተቃውሞ ቢያቀርቡም ይባስ ብለው እነ ኩማ ካድሬውን ለማሳመፅና አቅጣጫ ለማስቀየር በሚል ለመለስ ክስ እንዳቀረቡባቸውም ምንጮቹ ጨምረው አስረድተዋል።

በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የወያኔ ባለስልጣናት ምስጢራዊ ግምገማ አራት ኪሎ በሚገኘው በኢህአዴግ ጽህፈት ቤት እና በመለስ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ እያደረጉ ሲሆን የሬዲዮም ሆነ የቲሌቪዥን ጋዜጠኞች በቦታው እንዳይገኙ መከልከሉንም ምጮቹ አብራርተዋል።

የወያኔ ቡድን ከአድልኦና ከሙስና የጸዳሁ ነኝ እያለ ቢለፍፍም እየተሰራና እየተደረገ ያለው እውነታ ግን የተገላቢጦሽ መሆኑን ከተለያዩ ተቋዋሞች የደረሱን ጥቆማዎች ገለፁ።

ወያኔ በቅርቡ በአረብ ሀገራት ውስጥ የተፈጠረውን የፖለቲካ ቀውስን ተከትሎ ለመለስ ለሚቀርቡ ባለስልጣናት በምስጢር ውስጣዊ የስራ ክፍፍል ከመስጠቱም በተጨማሪ ዋና ዋና የተባሉ የሀገሪቱን ቁልፍ ቦታዎች በአንድ ወገን ብቻ እንዲያዝ ማደረጉን ከመከላከያና ከፌዴራል ፖሊስ የውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

እንደ ምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በአዲስ መልክ የፌዴራል ፖሊስን እና የመከላከያን ቁልፍ ቦታ ለህወሀት ባለስልጣናት እንዲይዙ ከማድረጉም በተጨማሪ ከህወሀቶችም መሀከል የራሴ ናቸው የሚላቸውን መርጦ ቁልፍ ቁልፍ ቦታ እንደሰጣቸው አጋልጠዋል።

ከዚህ ቀደም የመከላከያ የበላይ አዛዥና አድራጊ ፈጣሪ የሆነው ጄኔራል ሳሞራ የኑስ በጦር ኃይሎች ኤታማዦር ሹምነት ሲሰራ የነበረ ቢሆንም አሁን ደግሞ በተጨማሪ የቤተ መንግስት ዙሪያ ጥበቃን በበላይነት እንዲቆጣጠር በመለስ መመደቡን ምንጮቹ ገልፀዋል።

በህወሀት ክፍፍል ወቅት የነ ስዬ ቡድን ደጋፊ እንደነበረ የሚነገርለት እና ንስሀ ገብቶ ወደ እነ መለስ የተቀላቀለው ሌ/ጄ/ል ታደሰ ወረደ ከትምህርትና ስልጠና መምሪያ አዛዥነት በተጨማሪ ሙሉ ለሙሉ የምድር ኃይል ዋና አዛዥ ሆኖ እንዲሰራ መመደቡን ምንጮቹ ጠቁመዋል።

በህወሀት ክፍፍል ወቅት ከአየር ኃይል አዛዥነት የተነሳው ሜ/ጄ/ል አበበ ተክለሀይማኖት ምትክ የኦህዴዱ ሜ/ጄ/ል አለምሸት ደግፌን እንዲቆጣጠር ከስሩ ተመድቦ የነበረው ሜ/ጄ/ል ሞላ ኃይለማርያም በቅርቡ የአየር ኃይል ዋና አዛዥ ሆኖ የጸደቀለት ከመሆኑም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ በአየር ለሚንቀሳቀስ ወታደራዊ ሄሊኮፕተርም ሆነ ጄቶች የኦፕሬሽን ክፍል የበላይ ተቆጣጣሪ እንዲሆን መደረጉን ምንጮቹ ገልፀዋል።

ከዚህም ሌላ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉት የወታደራዊ ማሰልጠኛ የጦር ካምፖች ሙሉ ለሙሉ ከበረሀ በመጡ በህወሀት ሰዎች እንዲያዝ መደረጉን ያጋለጡት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ከመጋቢት አንድ ቀን ጀምሮ አዲስ ምስጢራዊ ምደባ እንደወጣም አጋልጠዋል።

በመከላከያ ውስጥ ያለው አደረጃጀት ከመቶ መሪ እስከ ክፍለ ጦር አዛዥነት ድረስ የህወሀት መኮንኖች ብቻ እንዲይዙት በመደረጉ ሰራዊቱ ተቃውሞ ሲያቀርብ የነበረ ቢሆንም አሁን ደግሞ የበለጠ ሙሉ ለሙሉ እነሱው እንዲይዙት በመደረጉ ውስጥ ውስጡን እያጉረመረመ እንደሚገኝም ምንጮቹ አስረድተዋል::

የፌዴራል ፖሊስ በበኩሉ በቅርቡ በምስጢር ባወጣ አዲስ ምደባ ከኮሚሽነሩ ወርቅነህ ገበየሁ በስተቀር በሙሉ ዋና ዋና ቦታዎች በህወሀት ሰዎች እንዲያዝ መደረጉ ታውቆዋል::

በህወሀት ክፍፍል ወቅት የአንጃው ቡድን አባል የነበረውና እራሱን ጥፋተኛ ነኝ ብሎ ይቅርታ ጠይቆ ከአባይ ፀሀዬ ጋር ተመልሶ ወደ እነ መለስ ቡድን የተቀላቀለው  ሀሰን ሽፋ ከዚህ ቀደም ምክትል ኮሚሽነር ሆኖ ከሚሰራበት በተጨማሪ የፖሊስ ኮሌጅ የበላይ ተቆጣጣሪ እንዲሆን መደረጉ ታውቆዋል::

በቅርቡ ለፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ መኮንኖች የማዕረግ እድገት በተሰጠበት ወቅት ያለ አንዳች ችግር የእጥፍ እድገት የተሰጣት ጄኔራል አለምጸሀይ የተሰኘችው ግለሰብ የፌዴራል ፖሊስ የአድማ ብተና ክፍል ኃላፊ ስትሆን ከመለስና አዜብ ጋር እጅግ የቀረበ ግንኙነት ያላት እንደሆነም መንጮቹ አጋልጠዋል::

በቅርቡ የፌዴራል ፖሊስ መኮንኖችን እና አባሎችን መቆጣጠሪያ ይሆናል የተባለው የኢንዶክትሪኔሽን መምሪያ ኃላፊ ረዳት ኮሚሽነር ጄኔራል በይዳ ገብራይ የተባለውም ከበረሀ የመጣ የህወሀት ካድሬ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ሁሉም ግለሰቦች ከአንድ ፓርቲ የተውጣጡ ከመሆኑም በላይ ለመለስ ዜናዊ የቀረቡ መሆናቸው ሌላው መስፈርት እንደሆነም አጋልጠዋል::ምንም እንኳዋን ለኮታ ማሙያ  የኦህዴዱ ወርቅነህ ገበየሁ ኮሚሽነር ተብሎ በቦታው ቢቀመጥም ከስሩ ያሉት ፀሀፊዎቹ የህወሀት ሰዎች መሆናቸው ታውቆዋል::

ለብዙ ዓመታት የፌዴራል ፖሊስ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሆኖ ሲሰራ የነበረውና በአሁኑ ሰዓት ወደ እንግሊዝ ጠፍቶ ጥገኝነት የጠየቀው ኮማንደር ደምሳሽ ኃይሉ ምትክ የቃሊቲ እስር ቤት አዛዥ የነበረው ኮሎኔል አበበ ዘሚካኤል የተባለው የህወሀት ካድሬ ቦታውን እንዲይዘው መደረጉን ምንጮቹ ገልፀዋል::

በሌላ ዜና እስከ ዛሬ ድረስ እልባት ያልተገኘለት  ከ200 ሺህ በላይ የሀገሪቱ ዜጎች ደማቸውን አፍስሰው..... አጥንታቸውን ከስክሰው...... አካለ ጎዶሎ ሆነው  የሞቱበትን የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የድንበር ግጭት አይደለም ሲል እብሪተኛው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ መናገሩ ህዝቡንና ሰራዊቱን እንዳበሳጨ ታወቀ::

ወያኔና ሻዕቢያ በረሀ እያሉ ኢትዮጵያን ለማፈረስ ሲምሉና ሲገዘቱ የነበሩት ሁለቱ እብድ መሪዎች በፈጠሩት ግጭት ከ80 ሺህ በላይ ዜጎች የተሰውበትን ትልቅ ገድል አንኳዋስሶና አዋርዶ የድንበር ግጭት ሳይሆን ያለ መግባባት ነው በማለት እንደ ተራ ነገር መግለጫ መስጠቱ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ በስጭት መቀስቀሱ ታውቆዋል::

ኢትዮጵያ ዳር ድንበርዋ በሻእቢያ ተወረረ ድረሱልኝ በማለት ነጋሪት እየጎሰመ ዜጎችን እሳት ውስጥ ሲከት የኖረው እብሪተኛው የወያኔ መሪ መለስ በቅርቡ ለኤርትራ ተቃዋሚዎች ልሳን በሰጠው መግለጫ አንኩወስሶ እና ገድሉን አዋርዶ በመናገሩ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ቁጭትን ያጫረ መሆኑ ታውቆዋል::

ከሻዕቢያ ጋር በረሀ በነበሩበት ወቅት የተፈጠረን አለመግባባት ስልጣን ላይ ከወጡ በሁዋላ በተከሰተ የጥቅም ግጭት የድንበር መጣስ አስመስሎ በማቅረቡ እጅግ ብዙ ዜጎች ከመሞታቸውም በተጨማሪ አካለ ጎዶሎ ሆነው ዛሬ በየቤታቸው ያለ ድጎማና ደጋፊ የቀሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች ባሉበት በዚህ ወቅት ታሪኩን ክዶና ሽምጥጦ ግጭቱ የጥቅም እንጂ የድንበር አይደለም በማለት ያለ አንዳች ሀፍረት መናገሩ የሰራዊቱን አባሎች ጭምር ያበሳጨ መሆኑ እየተነገረ ይገኛል::

ሰሞኑን የኤርትራ ተቃዋሚ ኃይሎች ልሳን ከሆነው «አሰና» ከተሰኘው ሚዲያ ጋር ቃለ ምልልስ ባደረገበት ወቅት እንደተናገረው ከሆነ ከሻዕቢያ ጋር የነበረው ግጭት የድንበር ሳይሆን የቆየ እና ስር የሰደደ በረሀ ያመጣው ችግር ነው ብሎ መናገሩም ተደመጦዋል::

ምንም በማያውቁት ጉዳይ በድንበር ሰበብ ተታልለው የተሰውት ኢትዮጵያውያን ደም ከንቱ መሆኑን የተናገረው ይሄው ግለሰብ አሁንም በለመደው መንገድ ወደ ኤርትራ ለመዝመትና ዜጎችን ለማስጨረስ አዲስ እቅድ እንደያዘም ተጠቁሞዋል::

በአሁኑ ሰዓት ወያኔ በፈጠራቸው ስግብግብ ድርጊቶች የተነሳ ህዝቡ በኑሮ ውድነት እየተሰቃየ ባለበት በዚህ ግዜ ለዜጎች ድጎማ ከማድረግ ይልቅ ለኤርትራ ተቃዋሚዎች ከፍተኛ ገንዘብ መመደቡ የሚያሳዝን እና የሚያሳፍር መሆኑንም ህዝቡ በቁጭት እየገለፀ ይገኛል::

በመጨረሻም ታሪክ በራዥ እና ከላሽ የሆነው የወያኔ ቡድን ጀግኖች አባቶቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት የተገኘውን የአድዋን ድል ለመንኩዋስስ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ታወቀ::

የህወሀት ከፍተኛ ባለስልጣኑ የሆነው ስብሀት ነጋ አራዳ ጊዮርጊስ የሚገኘው የአፄ ምኒልክ ሀውልት የአድዋ ድልን አያመለክትም ሲል በይፋ መግለጫ መስጠቱ በህይወት ያሉ ጀግኖች አባቶችን ብሎም መላ የሀገሪቱን ዜጎች ያሳዘነ መሆኑ ታወቀ::

ከደደቢት በረሀ ተሰባስቦ እንደ ግመሬ ዝንጀሮ ሲፈረጥጥ የመጣው የወያኔ ቡድን ከተመሰረተከ 36ኛ ዓመቲን አከበርኩ እያለ ሌት ከቀን እያናፋ ባለበት በዚህ ወቅት ለአፍሪካ ህዝብ ጭምር ኩራት እና የጥቁር ህዝቦች መገለጫ የሆነውን የአድዋ ድል ለመጨፍለቅና ጨርሶ ደብዛው እንዲጠፋ ለማድረግ እየተራወጠ መገኘቱ በእጀጉ ሚያሳዝን እና የሚያሳፍር የእብዶች አመለካከት ነው ሲሉ አባቶች በንዴት እየተናገሩ ይገኛሉ::

የጀግኖች ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን አኩሪ ጀግንነት መገለጫ የአፍሪካ ህዝብ ኩራት የሆነውን የአፄ ምኒልክ መታሰቢያ ሐውልት የአፍሪካ ርዕሰ መዲና ከሆነችው ከአዲስ አበባ እንዲነሳና ወደ አድዋ እንዲሄድ ከፍተኛ አፍራሽ ቅስቀሳ እያደረገ የሚገኘው የህወሀቱ ቁንጮ የሆነው ስብሀት ነጋ የአድዋ

ታሪክ አድዋ ላይ እንጂ አዲስ አበባ ላይ አይደለም ሲል መናገሩ ዛሬም ሀገር ማፍረስ የጀመሩት ስራ እንዳልተቋዋጨ የሚያሳይ ነው ሲል ህዝቡ  እየገለፀ መሆኑ ታውቆዋል፡፡